# ደህና ዋይ እማማ

አዬ፣ እማምዬ፣ ደህና ዋይ
ያሳወረሽ አሳወረኝ ፣ ቀን የተጣባብን ሥራይ፤
ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ...
ያለ ጠር መጣረር ዕዳ ፣ወይ ያለባላንጣ ግዳይ፤
አቆላልፎን ፣ አቆራርጦን፣ በእንባ በትካዜ ብካይ
ዘመን የተፋው ሾተላይ
አዬ፣ በቃሽኝ፤ በቃሁሽ፣ ዓይኔስ ዓይንሽንም አያይ...
በቃ እማማ እናት አለም፣እማትነፍጊ እማታቅማሚ
እማታሳጪ እማታሚ
እኔን በራበኝ፣ በጠማኝ፣ እንዲያ አብረሽኝ ስትጠሚ
ምነው ወተቴን ከጡትሽ፣ በጊዜ--ገፊ ታስቀሚ?

አንጀቴ ያንጀትሽ ቁራጭ
አጥንቴ ያጥንትሽ ፍላጭ
ሕይወትሽ የሕይወቴ ምንጭ፤ ወዜ የፍቅርሽ ወዝ ምጣጭ
ማህጸንሽ የፍጥረቴ አማጭ...
ከንግዲህ በቃሁሽ በቃኝ እማማ የነፍሴ ቁራጭ
ይበጠስ ውልሽ ከውሌ፣ ቃሌ ከቃልሽ ይፈለጥ
ዓይንሽ ባይኔ ትል ዘነበ፣ በቃኝ የኔው ብሌን ይፍረጥ
ብቻ በምን አንጀቴ ነው፣ አንጀቴን ባንጀቴ እምቆርጥ?
ይቆረጥ እንበል፣ ይገርሰስ?
ይረሳ፣ ይሙት፣ ይደምሰስ?
እርም አፈር እንበል ይበጠስ?
ማህጸንሽ ጽዋው መረዘኝ፣ ዘጠኝ ወር ያጠባኝ ገንቦ
ጡትሽ የደም ወተት ዘንቦ
ሆድሽ የቁስል ምጥ ታልቦ
ባዳ ቅሪት ተመትሮበሽ፣ የአንብርቴ እልባት ተሰብሮ
ደሜ በፋፋበት እትብት፣ ገፊ ዲቃላ ተቋጥሮ

በቃ እማማ፣ እማምዬ
መቀነቴ፣ ገበናዬ
በቃሁሽ አድባሬ፣ መቅኔ
ከንግዲህስ ላንቺ መጥኔ
አዬ ላንቺ አዬ ለኔ...
ጫቅላዬን ባዘለ እቅፍሽ
ገፊ ጉግ ማንጉግ መፅነስሽ
ነምቱ ሾተላይ ማብቀልሽ...
አይሆንም እንጂ ከሆነልሽ፣ ካለልሽ ካዘለቀልሽ
እግዚአብሄር ያሳድግልሽ፣
አዎን፣ ቃል ለምድር ለሰማይ

ደህና ዋይ፣ በቃ፣ ደህና ዋይ
ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ፤
ከፉም በጎም አናሰማ
እንዲያው ደህና ዋይ እማማ
እናተ አለም የስሜ አርማ
የህይወቴ ወዝ የአይኔ ማማ
እትነፍጊ እማታቅማሚ
እማታሰጭ እማታሚ
እኔን በራበኝ በጠማኝ አብረሽኝ እምትጠሚ
ጥቃቴን እምትጠቂ፣ ቁስሌን እምትታመሚ
ፍስሃዬን፣ ፈገግታዬን፣ ሳቄን ብቻ እምታልሚ
አንቺ እማማ
አንቺ የነፍሴ ዓልማ
የዓይኔ ማማ....
ምነው ጡትሽ ተጣረረኝ?
በጊዜ- ገፊ ለወጠኝ?
እንዴት ይንጠቀኝ ሾተላይ?
ቀን የተጣባብን ሥራይ
ያለኝታ ህብስተ-መና፣ የወገን ያጥንቴን ሲሳይ
የደሜን ምንጭ የሕይወቴን ማይ
የማህፀን የእትብቴን አዋይ?...
አዎን፤ ይብቃን እናት አለም፣ አንጀቴ ባንጀቴ ይቁረጥ
አጥንቴም በአጥንቴ ይድፈጥፈጥ
ቃሌም ከቃልሽ ይፈለጥ
የዓይኔም ውሃ በዓይንሽ ይፍረጥ
ይረሳ፣ ይጥፉ፤ ይደምሰስ
እርም አፈር እንበል ይበጠስ...
በቃ እማምዬ ደህና ዋይ
የደሚ ምንጭ የህይወቴ ማይ
የማህፀን የእትብቴ አዋይ
አሜን ቃል ለምድር ለስማይ
ዓይኔ ዓይንሽንም አያይ።

1953 ሎንዶን